SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

2ki Diro Kiiro 21

Hawaasa, Sadaasa 23, 2014 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፳፩

ሀዋሳ፣ ታህሳስ ፳፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም

<u>**Amado**</u>

Lallawu Kiiro 21/2014

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Mootimmate Loosaasine Lallawa … Qoola ….

<u>**ማውጫ**</u>

አዋጅ ቁጥር ፳፩/፳፻፲፬

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ… ገጽ ….

Lallawu Kiiro 21/2014

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Mootimmate Loosaasine Lallawa

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma safantunkunni harancho yanna ikkasinni mootimmate loosaasine gashshooti hajora albi qoqqowi lallawi kiiro 175/2011 loosu aana hosasi sufantanno gede lallawu kiiro 8/2012 fajjineenna horonsi'nanni hee'noonniha ikkirono xaa yannara qoqqowu umisi hattono gobboomu soorro hedote giddo worinoha mootimmate loosaasine gashshate seera fushsha hasiisinohura;

Mootimmate owaante uynanni gara yanna yannatenni woyyeessatenni owaatamaanno dagoomi kasseenya lossate dandiisiisanno mootimmate

አዋጅ ቁጥር ፳፩/፳፻፲፬

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ከመሆኑ የተነሳ ለመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ጉዳይ የነባሩ ክልል አዋጅ ቁጥር 175/2011 ሥራ ላይ መዋሉ እንዲቀጥል በአዋጅ ቁጥር 8/2012 ተፈቅዶ ሲሰራበት የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ክልሉ የራሱን እንዲሁም ሀገራዊ ለውጦችን ታሳቢ ያደረገ የመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በየጊዜ በማሻሻል የተገልጋዮን ህብረተሰብ እርካታ ለማሳደግ እንዲቻል በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የሰው ኃይል የሚሟላበት፣ የሚሰማራበትና

Mittu Waagi ….
ያንዱዋጋ

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

uurrinshubba giddo mannu wolqa wonshate, bobbahisatenna xa’misiisate xaphooma amuraate wora yannitenna hasiissannota ikkitinohura;

Mootimmate loosaasine loosinsa aana keeshshitanno gede assatenna haaro loosaasineno mootimmate looso baxxenna ammante loosatenni gumaamimma halashshate woyyaawino loosu qooxeesa kalaqa hasiissinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bayriidi Seera quwa 48 cinaancho quwa 3 (a) garinni aane nooha lallanboonni.

GAFA MITE

XAPHOOMA WORO

1. **Harancho Umo**

   Konne lallawa “Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Mootimmate Loosaasine Lallawa Kiiro 21/2014” yine woshshinara dandiinanni.

2. **Tiro**

   Horonsi’noonni gari wole tiro uyisiisannoha ikka hoogiro konni lallawi giddo:

   1. **“Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
   2. **“Biiro woy Biirote Sooreessi”** yaa aantensa garinni Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biirootinna Sooreessaati.

የሚጠየቅበትን አጠቃላይ ሥርዓት ማስቀመጥ ወቅታዊና አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንግሥት ሠራተኞች በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ለማድረግና አዳዲስ ሠራተኞችም የመንግሥትን ሥራ ወደውት እና አምነውበት በመሥራት ፍሬያማነትን እንዲጨምሩ የተሻለ የሥራ አከባቢ መፍጠር በማስፈለጉ፤

በሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሀ) መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ “የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር ፳፩/፳፻፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡
   2. **“ቢሮ ወይም ቢሮ ኃላፊ”** ማለት እንደየቅደም ተከተሉ የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ እና ቢሮ ኃላፊ ነው፡፡
   3. **“የመንግሥት መሥሪያ ቤት”** ማለት ራሱን

3. **“Mootimmate Loosu Mine”** yaa umosi dandee lallawunni woy wodhotenni tantaname wo’munni wo’ma woy boco mootimmatenni gaammanni baajeettenni galanno Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma loosu mineeti.

4. **“Mootimmate Loosaasincho”** yaa qoqqowu mootimma loosu mini giddo uurrinshunni qaxarame loosannoha ikkeenna konni woroonni noore dihanqafanno:

   a) Mootoonsinoonnire,

   b) Deerru deerrunkunni dagate riqiwamaano ikkite mootimmate loosu minnara qaxarante loossannokkire,

   c) Deerru deerrunku heedhanno yooaanonna seeru allaalaano,

   d) Poolisete miillanna poolisete wodhonni galtanno loosaasine,

   e) Wole hajo la’anno seerinni konni lallawinni galtannokki gede assinoonni loosaasine.

5. **“Yannate Geeshshi Loosaasincho”** yaa mootimmate loosu mine uurrinsha afi’rinokki woy yannate geeshshi looso jeefisate uurrinshu loosu madawera yannate geeshshira qaxarame loosanno ogeessa ikkeenna konni woroonni noore dihanqafanno:

ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመና ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር የክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው::

4. **“የመንግሥት ሠራተኛ”** ማለት በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ሲሆን የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

   ሀ) የመንግሥት ተሿሚዎችን፣

   ለ) በየደረጃው የሕዝብ ተወካይ ሆነው በመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥረው የማይሰሩን፤

   ሐ) በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤት ዳኞችንና ዐቃቤ ሕጎችን፣

   መ) የፖሊስ አባላትና በፖሊስ ደንብ በሚተዳደሩ፤

   ሠ) ሌሎች አግባብነት ባለው ሕግ በዚህ አዋጅ እንደማይተዳደሩ በተመለከቱ ሠራተኞች::

5. **“ጊዜያዊ ሠራተኛ”** ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባሕርይ የሌለውን ወይም ጊዜያዊ ሥራ ለመፈጸም በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ሲሆን የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

   ሀ) በቀን ሂሳብ እየተከፈላቸው የሚሠሩ የቀን ሠራተኞችን፤

   ለ) በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ለሙያ መልመጃ ወይም ለተግባር ሥልጠና የተመደቡ ሰዎችን፤

   ሐ)ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በሚገቡት ውል መሠረት ዋጋ እየተከፈላቸው በራሳቸው የንግድ ሥራ ወይም የሙያ ኃላፊነት

a) Barru baatooshshe baantanna loossanno barru loosaasine,

b) Mootimmate loosu mini giddo ogimma rosiisi’rate woy loosu aani qajeelshira gaamantinore,

c) Mootimmate loosu mini giddo sheemaatu garinni baantannansa ogimmate looso loossannore ikkite uminsa looso loosidhe galtannore,

d) Addi ogimmanna dandoonsa kaiminni mootimmate loosu mini ledo e’anno sheemati garinni hasiisannore baantannansa tirfe yannansanni loossanno loosaasine.

6. **“Aliidi Sooreessa”** yaa mootimmate loosu mine aliidimmate massagannoho woy lekkisaanchoho;

7. **“Loosu Madawe”** yaa mittu mootimmate loosaasinchi wo’ma loosu yannasinni loosanno gede biilloonyu noonsa bissanni uynoonni loosu qeechanna biilloonyeeti.

8. **“Deerru Lopho”** yaa mootimmate loosaasincho amadino loosu deerrinni gotti yino loosu deerrira lossate.

9. **“Ikkadimma Buuxate Amanyoote”** yaa mootimmate loosaasinchi woy haaro qaxaraminohu loosanno woy qaxaramino madawera ikkadimmasi buunxanni amanyooteeti.

10. **“Damooza”** yaa mittu loosu deerrira

የሚሠሩ ሰዎችን፤

መ) ባላቸው ልዩ እውቀትና ችሎታ ምክንያት ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር በሚገቡት ውል መሠረት ዋጋ እየተከፈላቸው በትርፍ ጊዜያቸው የሚሠሩ ባለሙያዎችን፡፡

6. **“የበላይ ኃላፊ”** ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤትን በበላይነት የሚመራ ወይም ምክትል ነው፡፡

7. **“የሥራ መደብ”** ማለት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ሙሉ በሥራ ጊዜዉ እንዲያከናዉን ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ተግባርና ኃላፊነት ነው፡፡

8. **“የደረጃ ዕድገት”** ማለት የመንግሥት ሠራተኛን ከያዘው የሥራ ደረጃ ከፍ ወዳለ የሥራ ደረጃ ማሳደግ ነው፡፡

9. **“የብቃት ማረጋገጫ ስርዓት”** ማለት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም አዲስ ተቀጣሪ ሰው ስለተመደበበት ወይም ስለሚቀጠርበት የሥራ መደብ ብቁ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት ስርዓት ነው፡፡

10. **“ደመወዝ”** ማለት በአንድ የሥራ ደረጃ ለተመደቡ ሥራዎች የተወሰነ መነሻ ክፍያ ወይም የእርከን ክፍያ ነው፡፡

11. **“የሥራ ሁኔታ”** ማለት በመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በመንግሥት ሠራተኞች መካከል ያለ ጠቅላላ የሥራ ግንኙነት ሲሆን ይህም የሥራ ሰዓትን፣ ደመወዝን፣ ልዩ ልዩ ፈቃዶችን፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነትን፣ የሠራተኞች የሥራ ስንብት ሁኔታና ክፍያን፣ የዲሲፕሊን አፈጻጸምና የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓቶችን እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

gaamantino loossara kaajjinshoonni kaimu woy gufote baatooshsheeti.

11. **“Loosu Akata”** yaa mootimmate loosu mininna loosaasinete mereero hee’rannoha xaphoomu xaadooshshe ikkeenna giddosi loosu yanna, damooza, addi addi fajjo, loosu qooxeessi fayyinaate, loosunni ittisate baatooshshe, amanyootu gumulonna koffeenya shiqishi’nanni garanna labbannore hanqafanno.

12. **“Dilidile”** yaa mootimmate loosaasincho taalu deerrinna damoozinni gotti yino deerrinna damoozira woy loosaasinchu sumuummenni heeshshi yino deerrira gaame loosiisate.

13. **“Amanyootu Qaafo”** yaa aye mootimmate loosaasinchi konne lallawanna lallawa jeefisate fultanno wodho hattono biddissubba woy loosaasinete amanyootu koodde sa’’atenni iillishanno hunaanchimmara uynanni qorchaati.

14. **“Koo-teemmate Seeyaanyo”** yaa loosu baycho kalaqaminoha ikkeenna, hasattote gobbaanni shiqqannoti siimu xaadooshshi hedo woy xa’mo woy hakka qolte xixxiibbanno qaalla woy mannimmatenni riiqata ikkeenna, konni woroonni nooreno hanqaffanno:

a) Fajjo nookkiha sunqa, riiqata, amammadanna hattoo garinni kikkisa;

b) Siimu xaadooshshi hasatto garinni

12. **“ድልድል”** ማለት አንድን የመንግሥት ሠራተኛ በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ ወይም ከፍ ባለ ደረጃና ደመወዝ ወይም በሠራተኛው ስምምነት ዝቅ ባለ ደረጃ መድቦ ማሠራት ነው፡፡

13. **"የዲሲፕሊን እርምጃ"** ማለት ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ወይም የመንግስት ሠራተኞች ሥነ-ምግባር ኮድ በመተላለፍ ለሚያደርሰው ጥፋት የሚወሰንበት ቅጣት ነው፡፡

14. **“ጾታዊ ትንኮሳ”** ማለት በሥራ ቦታ የሚፈጸም ሆኖ ከሌላው ወገን ፈቃድ ውጪ የሚቀርብ የወሲብ ሀሳብ ወይም ጥያቄ ወይም ሌላ ወሲባዊ ተፈጥሮ ያለው የቃል ወይም የአካል ንኪኪ ተግባር ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ)ከሌላው ወገን ፈቃድ ውጪ የመሳም፣ የሰውነት አካልን የመዳሰስ፣ የመጎንተል ወይም የመሳሰለውን የሰውነት ንክኪ የመፈጸም ድርጊት፤

ለ) ወሲብ አዘል በሆነ ሁኔታ ተጠቂውን መከታተል ወይም እንቅስቃሴውን መገደብ፤

ሐ)ለቅጥር፣ ለደረጃ እድገት፣ ለዝውውር፣ ለድልድል፣ ለሥልጠና፣ ለትምህርት፣ ለጥቅማ ጥቅሞች ወይም ማንኛውንም የሰው ሀብት ሥራ አመራር ተግባር ለመፈጸም ወይም ለመፍቀድ ወሲብን እንደ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ፣

ha'runsa, ea fula hoola;

c) Qixirete, deerru lophora, soorrishshaho, gaamooshsheho, qajeelshaho, rosoho, addi addi horubbara hattono mannu jiro massago loossara siimu xaadooshshe xa'ma.

3. Koo-teemmate Xawishsha

Mitte koo-teemmanni xawisnoonnihu hasiishshu garinni wole koo-teemmano hanqafanno.

4. Jeefishshu Mami-geeshsha

Konni lallawi jeefishshi "Mootimmate Loosu Mine" nna "Mootimmate Loosaasincho" yitanno tironni hanqafantanno loosu minnanna loosaasine aana wo'munni wo'ma jeefamannoha ikke "Yannate Geeshshi Loosaasincho" yitanno tironni hanqafamanno loosaasincho lainohunni lallawu quwa 21 worronni bikkinni calla jeefamannoha ikkanno.

GAFA LAME

MOOTIMMATE LOOSU MINI TANTANO, LOOSU KEENO, DAMOOZANNA HORAAMISHSHU BAATOOSHSHE

5. Mootimmate Loosu Mini Tantano

1. Aye qoqqowu mootimma loosu mini uynoonnisi looso jeefisate hasiissanno tantanonna mannu wolqa hasatto xiinxalle biirote shiqishe gumulsiisiranno.
2. Biiro qoqqowu jeefisiisaano loosu minna

3. *የጾታ አገላለጽ*

በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላዉንም ጾታ ያካትታል፡፡

4. ***የተፈጻሚነት ወሰን***

ይህ አዋጅ "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" እና "የመንግሥት ሠራተኛ" በሚል ትርጉም በሚሸፈኑ መስሪያ ቤቶችና ሠራተኞች ላይ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ሲሆን "ጊዜያዊ ሠራተኛ" በሚል ትርጉም የሚሸፈን ሠራተኛን በሚመለከት በአዋጁ አንቀጽ 21 በተደነገገው አግባብ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የመንግሥት መሥሪያ ቤት አደረጃጀት፣ የሥራ ምዘና፣ የደመወዝ ስኬል እና አበል

5. *የመንግሥት መሥሪያ ቤት አደረጃጀት*

ማንኛውም የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት የተቋቋመለትን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን አደረጃጀትና የሰው ኃይል ፍላጎት አጥንቶ ለቢሮው አቅርቦ ያስወስናል፡፡ ቢሮው የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችን አደረጃጀት አግባብነትና ውጤታማነት እያጠና ማሻሻያ ሲያስፈልግ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

6. ***የሥራ ምዘና***

1. *ቢሮው በአገር አቀፍ ደረጃ በሚወሰነው ተስማሚ የሥራ ምዘና ዘዴን በመንግሥት መሥሪያ ቤት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡*
2. *ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት*

tantano garimmanna gumaamimma xiinxallatenni woyyeessa hasiissuro qoqqowu gashshootu amaalete minira gumulote shiqishshanno.

6. **Loosu Keeno**

1. Biiro gobboomu deerrinni gumullanni garinni injiitanno loosu keeno hayyo mootimmate loosu minnara loosu aana hossanno gede assitanno.
2. Aye loosu mini deerransa gumulloonnikki haaro loosu madabba loosu tittiro qixxeessatenni biirote shiqishe deerransa gumulisiisiranno.
3. Loosu keenonna deerru gumulo gobboomu deerrinni worroonni faasho kaiminni qoqqowu gashshootu amaale mini fushshanno wodho garinni jeeffannoha ikkanno.

7. **Damoozu Deerra**

1. Biiro hasiisino yannara hajo la'annonsa bissaa ledo halamatenni damooza xiinxallanna ogimmate xawishsha aateni Qoqqowu Jeefisiisaanote Amaale Minira gumulote shiqishshanno; fajjiniro jeefishsha qorqortanno.
2. Damoozu mittu mittunku deerrihu kaimunna jeefo hattono yanna yannantenni assinanni ledo lainohunni giddaasinchu deerri hee'rannosi.
3. Qoqqowu mootimma latishshu uurrinshuwanna qoqqowu gashootu amaale

ደረጃቸው ያልተወሰነላቸው አዳዲስ የሥራ መደቦችን የሥራ ዝርዝር አዘጋጅቶ ለቢሮው በማቅረብ ደረጃቸውን ያስወስናል፡፡

3. የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚወሰነው ስርዓት ላይ ተመስርቶ የክልል መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

7. **ደመወዝ ስኬል**
   1. ቢሮው ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የደመወዝ ስኬል በማጥናትና ሙያዊ አስተያየት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፡፡
   2. የደመወዝ ስኬል ለእያንዳንዱ ደረጃ መነሻና መድረሻ ደመወዝ፣ እንዲሁም በየጊዜው የሚደረገውን የደመወዝ ጭማሪ የሚያመለክቱ እርከኖች ይኖሩታል፡፡
   3. የክልሉ መንግሥት ልማት ድርጅቶችና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በልዩ ሁኔታ የሚቋቋም ተቋም ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል የመንግሥትን የፋይናንስ አቅም፣ የህዝቡን አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ፣ የሥራ ደረጃዎች እና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሁኔታዎችን ባገናዘበ መንገድ በየጊዜው እየተጠና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚወሰን ይሆናል፡፡

8. **ለእኩል ሥራዎች እኩል ደመወዝ ስለመክፈል**

እኩል ዋጋ ያላቸው ሥራዎች ሁሉ እኩል መነሻ ደመወዝ ይኖራቸዋል፡፡

mininni baxxino garinni uurrinsanni uurrinshuwa loosaasine damoozu deerra, faynaansete wolqa, Dagannita heeshshote gara, loosu jilbanna xaphooma qoqqowu akata hedote giddo woratenni yanna yannatenni xiinxallatenni qoqqowu gasshshootu amaalete mininni gumullanniha ikkanno.

8. Taalu Loosira Taalo Damooza Baata

Taalo deerra afidhino loossa baalantera taalo kaimu damooza baantanni.

9. Damoozu Baatooshshe

1. Ayeehuno mootimmate loosu mini aganu goofimarchira loosaasinesira woy seeru riqiwaanosira damoozu baatooshshe baatanno.

2. Aye mootimmate loosaasinchi damoozi amadamara woy muramara dandaannoha:

   a) Loosaasinchi sumuummesi borrotenni xawisiro;

   b) Yoote mini hajajonni;

   c) Seerunni jeefinsoonni garinni kaajjinshoonniha ikkiro calla ikkanno.

3. Konni quwi cinaancho quwa 2 (b) woy (c) garinni loosaasinchu damoozi aaninni aganu aganunni murrannihu daamozunnita sasetenni mitte anga aleenni ikka dinosi.

9. የደመወዝ ክፍያ

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በየወሩ መጨረሻ ለሠራተኞቹ ወይም ለሕጋዊ ወኪሎቻቸው የደመወዝ ክፍያ ይፈጽማል፡፡
2. የማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዝ ሊያዝ ወይም ሊቆረጥ የሚችለው፡-

   ሀ)ሠራተኛው ስምምነቱን በጽሑፍ ሲገልጽ፣

   ለ) በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣

   ሐ) በሕግ በተደነገገው መሠረት ሲወሰን ብቻ ነው፡፡
3. በዚህ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ወይም (ሐ) መሠረት ከሠራተኛ ደመወዝ በየወሩ የሚቆረጠው ከደመወዙ አንድ ሦስተኛ አይበልጥም፡፡

10. አበል

1. ማንኛውም አበል የሚከፈለው የመንግሥትን ሥራ ለማከናወን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡
2. ቢሮው ከመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚቀርቡ የአበል ዓይነቶችን እና ክፍያዎችን እያጠና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀዱም አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፡፡

ክፍል ሦስት

<u>የሰው ሀብት ዕቅድ፣ ስምሪት እና የሥራ አፈጻጸም ምዘና</u>

ንኡስ ክፍል አንድ

10. Horaamishshu Baatooshshe

1. Ayehano horaamishshu baatooshshe baantannihu mootimmate looso loosate hasiisannoha ikkiro callaati.

2. Biiro mootimmate loosu mininni shiqqanno horaamishshu baatooshshubba xiinxallatenni qoqqowu gashshootu amaalete minira gumulote shiqishshanno; fajjiniro ha'rinsho qorqortanno.

GAFA SASE

MANNU JIRO MIXO, BOBBAASONNA LOOSU JEEFISHSHI KEENO

Cinaancho Gafa Mite

Filotenna Doorshu Amanyoote

11. Mannu Jiro Mixo

1. Mannu jiro mixo hexxo ayehuno mootimmate loosu mini massagaancho mixosi aana wodhino hexxo jeefisate, mannu wolqa hasatto jeefisate, hasiisanno mannu wolqa wonshate, latisate, hattono seerunni horoonsiratenna kuriuu irkissanno qaafo adhatenna gumano yanna yannatenni keennanni woyyeessateeti.

2. Aye mootimmate loosu mini massagaancho mixosi kaima assatenni harancho, mereerimanna seeda yanna mannu wolqa mixo xiinxalle loosu aana hosiisa noosi.

3. Fano loosu madawe loosaasinetenni

ምልመላና መረጣ

11. የሰው ሀብት ዕቅድ

1. የሰው ሀብት ዕቅድ ዓላማ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት በስትራቴጂያዊ ዕቅድ ላይ የተቀመጡትን ዓላማዎች ለማሳካት የሰው ሀብት ፍላጎት ለመተንበይ፣ የሚያስፈልገውን የሰው ሀብት በዓይነትና በብዛት ለማሟላት፣ ለማልማት፣ በአግባቡ ለመጠቀም የሚያግዙ እርምጃዎችን ለመውሰድና ውጤቱንም በየጊዜው እየገመገመ ማሻሻያ ለማድረግ ነው፡፡
2. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሰው ሀብት ዕቅዱን አጥንቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
3. ክፍት የሥራ መደቦችን በሠራተኛ ማስያዝ የሚቻለው የሰው ሀብት ዕቅድን መሠረት በማድረግ በደረጃ ዕድገት ወይም በቅጥር ወይም በዝውውር ወይም በድልድል ይሆናል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

12. ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤት የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት

1. ቢሮው በክፍት የሥራ መደቦች ላይ አመልካቾች ተወዳድረው ስለሚቀጠሩበትና ስለሚያድጉበት የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት መዘርጋት የሚያስችሉ መመዘኛዎችና መለኪያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀውን ተከትሎ በክልሉ በሚገኙ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

amadisiisa dandiinannihu mannu jiro mixo kaima assatenni deerru lophonni, qixiretenni, soorrishshunni woy dilidiletenni ikkanno. Tittiro biddissunni murranni.

12. Mootimmate Loosu Mine Eotenna Ikkadimmate Buuxo Amanyoote

1. Biiro qoqqowu giddo heedhanno fano loosu madawera heewisamaano heewotenni qaxarantannonna deerru lopho afidhanno eotenna ikkadimmate buuxo assinanni amanyoote diriirsate dandiisiissanno gobboomu deerrinni qixxaabbanno keenaasinchuwanna bikkaasinchuwa harunsatenni mootimmate loosu minnara loosu aana hosanno gede assitanno.

2. Keenaasinchuwanna bikkaasinchuwa loosu aana hossanno ikkito qoqqowu jeefisiisaanote amaalete mini fushshanno wodhonni murranni.

3. Konni quwi cinaancho quwa 1 aana worroonni eotenna ikkadimmate buuxo amanyoote jeefisiissanno uurrinsha uurrinsara dandiinanni.

13. Qixirete Jeefishsha

1. Lallawu garinni qaxara dandiitannori qoqqowu, zoonete, quchumu gashshootinna woradu mereershshu deerinni heedhanno sekitere mootimmate loosu minnati.
2. Qaxarate hasishshu, fano loosu madawenna baajete heerase hajo la’’anno loosu sooreessi buuxante borrotenni gumulama noose.

2. መመዘኛዎቹና መለኪያዎቹ ሥራ ላይ ስለሚውሉበት ሁኔታ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የመግቢያና የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓትን የሚያስፈጽም ተቋም ሊቋቋም ይችላል፡፡

13. ስለቅጥር አፈጻጸም

1. በአዋጁ መሰረት ቅጥር ለመፈጸም የሚችሉት በክልል፣ በዞን፣ በከተማ አስተዳደር እና በወረዳ ማዕከል ደረጃ የሚገኙ ሴክተር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ናቸው፡፡
2. ቅጥር ለመፈጸም አስፈላጊነት፣ ክፍት የሥራ መደብ እና በጀት መኖሩ ጉዳዩ በሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ተረጋግጦ በጽሁፍ መወሰን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተመለከተው መሰረት ሲወሰን ማስታወቂያ በማውጣት አመልካቾች እንዲመዘገቡ መጋበዝ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው ቢኖርም በገበያ ላይ እጥረት ባለባቸው ሙያዎች ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር ምሩቃንን በመጋበዝ ማወዳደር ይቻላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 መሠረት የሚቀጠሩ ምሩቃን የብቃት ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. የምልመላና መረጣ ሂደቶችን ያለፈ ተወዳዳሪ ቅጥር ተግባራዊ እንዲሆን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ተቋም ቅጥሩ እንዲጸድቅለት ለቢሮው

3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 iima xawinsonni garinni gumulliro egensiishsha fushshatenni heewisamaano borreessantanno gede koyisa hasiissanno.
4. Konni quwi conaanchu quwi 3 iima worronnihu heerirono dikkote anje noo oggimmara aliidi rosu uurrinshubba ledo xaadooshshe kalaqatenni maasirantanore koyisatenni heewisiisa dandiinanni.
5. Konni quwi cinaanchu quwi 4 garinni qaxarantanno maasamaano ikkadimmate buuxishsha shiqisha noonsa.
6. Filatenna doorshu ha'rinsho saino heewisamaano qixire jeefantanno gede konni quwi cinaanchu quwi 1 xawinsonni uurrinsha qixire wonsantanno gede biirote sowa nooseha ikkanna biirono gumulose 30 barri giddo borrotenni egensiisa noose.
7. Mootimmate loosaasine qixire jeefinsanni tittirshu ikkito amanyoote lainohunni biiro biddissa fushshitanno.

14. Filonna Doorsha

1. Filonna doorsha assinannihu qoqqowu deerrinni fushshinanni keenaasinchi garinni uyinanni fonqoli gumi woy wolu daninni buuxantino ogimmatenna loosu ikkadimma aana calla kaima assineeti.

2. Ayimmanna mayimma, koo-teemma, amma'no, politiku laooshshe, bisu gawajjo, HIV eedisi woy wole ikkitonni looso hasidhannori aana woy mootimmate loosaasine mereero babbadooshshe assa

መላክ ያለበት ሲሆን ቢሮውም ውሳኔውን እስከ 30 ቀናት በጽሁፍ ማስታወቅ አለበት፡፡

7. የመንግሥት ሠራተኞች ቅጥር አፈጻጸም ዝርዝር ሁኔታ ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡

14. ምልመላና መረጣ

1. ምልመላና መረጣ የሚደረገው በክልል ደረጃ በሚወጣ መመዘኛ መሰረት በሚሰጥ ፈተና ውጤት ወይም ሌላ ማናቸውም ዓይነት ተጨባጭ የሙያና ሥራ ብቃት ማረጋገጫ ላይ ተመስርቶ ይሆናል፡፡
2. በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ወይም በሌላም ሁኔታ በሥራ ፈላጊዎችም ሆነ በመንግሥት ሠራተኞች መካከል ልዩነት ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
3. በአዋጁ ከአንቀጽ 47 እስከ 50 የተጠቀሱት አዎንታዊ ድጋፍ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በክፍት የሥራ መደብ ላይ ሠራተኛ የሚመደበው ለሥራ መደቡ የሚጠየቀውን ተፈላጊ ችሎታ የሚያሟላና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር ተወዳድሮ ብልጫ ያለው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡

15. የመንግሥት ሠራተኛ ሆኖ ለመቀጠር የማያስችሉ ሁኔታዎች

1. የሚከተሉት የመንግሥት ሠራተኛ ሆነው ሊቀጠሩ አይችሉም፤
   ሀ) ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው፤

hoolloonnite.

3. Lallawu quwa 47 kayise 50 geeshsha jawaachishu irko assinara fajjinoonnihu agarame heereenna fano loosu madawera loosaasincho gaammannihu loosu madawe xa'mitanno hasiissanno ikkito wonshannohanna woloottu heewisamaano ledo heewisame roore leelliro callaati.

15. Mootimmate Loosaasincho Ikke Qaxarama Hoolisiissanno Ikkituwa

1. Mootimmate loosaasincho ikke qaxarama dandaannokkihu:

   a) Dirosi 18 ikkinokkihu;

   b) Muishshu, ammanama xeisate, mooru, sarraaqate woy wolqatenni giddeesse seyaatate jaddonni Yoote Mine hunaanchimmasi buunxe qorichinshoonni manchi uynoonnisi qoricha gudinkunni woy yirgunni uurrinkunni woy maaro assinihu gedensaanni onte diro sainosikkihu;

   c) Ikkadimmate dandoo buuxissanno taje noosikkihu;

   d) Lallawu garinni qaxaramanno woyite qaalu woyyo eate umosi fajjannokkihu.

2. Konne quwa cinaancho quwa 1 (b) woro agarante heedheenna mootimmate loosu mininni disipiliinete xe'nenni shorramino manchi shorrami yannanni kayise ontu diri wo'ma geeshsha mootimmate

ለ) ቅጣቱ ከተፈጸመ፣ በይርጋ ከታገደ ወይም በይቅርታ ከተሠረዘ በኋላ አምስት ዓመት ያለፈው ካልሆነ በስተቀር የሙስና፣ የእምነት ማጉደል፣ የስርቆት፣ የማጭበርበር ወይም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈጽሞ ፍርድ ቤት የተፈረደበት ሰው፤

ሐ) የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የሌለው ሰው፤

መ) በአዋጁ አንቀጽ 17 መሠረት ቃለ መሀላ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት በዲስፕሊን ጉድለት ከሥራ የተሰናበተ ሰው ከሥራ ከተሰናበተበት ጊዜ ጀምሮ አምስት ዓመት ከመሙላቱ በፊት በመንግሥት ሠራተኛነት ሊቀጠር አይችልም።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አመልካች በመንግሥት ሥራ ተቀጥሮ ለማገልገል ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምርመራ በስተቀር የጤንነት ማረጋገጫ የሕክምና ምርመራ እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ለ) ከተጠቀሱት ወንጀሎች ነጻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከፖሊስ የተሰጠ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት በላይ የሆናቸውና አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ወጣቶች

loosaasinchimmara wirro qaxarama didandaanno.

3. Konne quwa cinaancho quwa 1 (c) woro agarante heedheenna aye manchino mootimmate loosu mine qaxarame loosate ikkado ikkasi buuxate HIV/AIDIS gobbaanni keeraanchimmasi buuxate hakimete taje hattono konne quwa cinaancho quwa 1 (b) aana xawinsoonni jaddonni keeraancho ikkasi buuxisiissanno Poolisete mininni uyinoonni taje abbate gadacho heedhannosi.

4. Konni quwi cinaanchu quwi 1(a) aana worroonniha noowa heereenna dirinsa 14 aleenni ikke 18 wo’minonsakki wedelli qaxarantannonna loosu ikkito lainohunni biiro biddissa fushshitanno.

16. Wole Gobba Qansooti Qaxarantanno Amanyoote

Itophiyaho ilantino wole gobba qansoota addi addi qoosso horaameeyye assate fulino lallawi kiiro 270/1994 quwa 5 (2) hattono konni lallawi quwa 21 cinaancho quwa (2) worroonnihu agarame hee’reenna Itophiyu qansicha ikkinokkihu mootimmate loosaasincho ikke qaxarama didandaanno.

17. Qaalu Woyyo Ea

Dooramino heewisamaanchi mootimmate loosu mine looso hanafara albaanni xaare qaale ea noosi.

Eanno qaalu gondoorino:

ስለሚቀጠሩበትና ስለሥራ ሁኔታቸው ቢሮው መመሪያ ያወጣል፡፡

16. የውጭ አገር ዜጎች ቅጥር

ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 አንቀጽ 5(2) እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21(2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ሰው በመንግሥት ሠራተኛነት ሊቀጠር አይችልም፡፡

17. ቃለ መሐላ ስለመፈጸም

የተመረጠው አመልካች ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ መሐላ ይፈጽማል፤

“እኔ ……………… በመንግሥት ሠራተኛነቴ ከሁሉም በላይ አድርጌ በእውነት፣ በታማኝነትና ሥነ-ምግባር ሕዝብን ለማገልገልና የመንግሥትን ፖሊሲዎች ለመፈጸም፣ በማንኛውም ጊዜ ሕገ መንግሥቱንና የአገሪቱን ሕጎች ለማክበር እና በሥራዬ ምክንያት ያወቅሁትንና በሕግ ወይም በሚመለከተው አካል ውሳኔ በምስጢርነት የተመደቡትን ለሌላ ለማንኛውም ወገን ላለመግለጽ ቃል እገባለሁ፡፡”

18. የመቀጠሪያ ደመወዝ አወሳሰን

ማንኛውም አዲስ ተቀጣሪ የመንግሥት ሠራተኛ በመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል መሠረት ለተቀጠረበት የሥራ መደብ የተወሰነው ደረጃ መነሻ ደመወዝ ይከፈለዋል፡፡

Ani su'ma'ya …………….. yaamameemmohu motimmate loosaasinchimma'yanni wo'munkunni aleenni asse halaalunni, ammanamatenninna amanyootunni dagate soqqamatenna mootimmate seerubbano garunni gumulate aye yannarano gobbate aliidi seeranna woloota seerubba ayiirrisate hattono konni loosi widoonni afeemmo seerubbanna addi addi fojo hajo la'annonsakki bissara sayise aa hoogate qaale e''eemmo.

18. Qaxarammanni Damooza Muranni Gara

Haaru garinni qaxaramannohu mootimmate loosaasinchi mootimmate loosaasine qaxarate worroonni giddaasinchira noo garinni qaxarami madaweha kaimu damooza baantannisiha ikkanno.

19. Wo'naalshu Yanna

1. Wo'naalshu yannati guulcho hedo haaru garinni qaxaraminohu mootimmate loosaasinchi loosu jeefishsha harunsonna irko assinannasi ikkadimmasi buuxateeti.

2. Dooramino heewisamaanchira madawete su'ma, deerranna damooza, hattono looso hanafanno barra xawissannota wo'naalshu yanna xawissanno borro loosu mini sooreessinni woy loosaasine qaxarate riqiwo uyinoonni sooreessinni sumundoonni borro loosanno loosu tittiro xawishshi ledo uyinanni.

3. Loosaasinchu wo'naalshu yannara qaxarami loosu madawera leyu agani keenonni

19. የሙከራ ጊዜ

1. የሙከራ ጊዜ ዓላማ አዲስ የተቀጠረ የመንግሥት ሠራተኛ ስለሥራ አፈጻጸሙ ክትትል እየተደረገ ብቃቱን ለማረጋገጥ ይሆናል፡፡
2. የተመረጠው አመልካች የሥራ መደቡን መጠሪያ፣ የተመደበበትን ደረጃ፣ ደመወዙንና ሥራውን የሚጀምርበትን ቀን የሚገልጽ በአሠሪው መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ወይም ሠራተኛን ለመቅጠር ውክልና በተሰጠው የሥራ ኃላፊ የተፈረመ የሙከራ ቅጥር ደብዳቤ በሥራ መደቡ ከሚያከናውነው የሥራ ዝርዝር መግለጫ ጋር ይሰጠዋል፡፡
3. የሠራተኛው የሙከራ ጊዜ በተቀጠረበት የሥራ መደብ ላይ ለስድስት ወር ሆኖ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ ከመካከለኛ በታች ሆኖ ከተገኘ የሙከራ ጊዜው ለተጨማሪ ሦስት ወር ሊራዘም ይችላል፡፡
4. በተራዘመው የሙከራ ጊዜ ውስጥ ሠራተኛው መካከለኛ ወይም ከዚያ በላይ የተጠቃለለ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ካላገኘ ከሥራ ይሰናበታል፡፡
5. የአዋጁ አንቀጽ 59(3) እና (4) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሙከራ ላይ ያለ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ ወይም በሥራ ላይ በሚደርስ አደጋ ምክንያት ከሥራ የቀረ እንደሆነ ያልጨረሰውን የሙከራ ጊዜ ከሕመሙ ወይም ከጉዳቱ ከዳነበት ጊዜ አንስቶ እንዲጨርስ ይደረጋል፡፡
6. በሙከራ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ሠራተኛ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት

mereerimunni ajino guma abbiro sasu aganira wo'naalshu yannasi lende seedinsanniha ikkanno.

4. Seedinsoonni yanna giddo loosaasinchu jawaate loosatenni mereerimanna hakkuyi aliidi guma abba hoogiro loosunni shorramannoha ikkanno.

5. Konni lallawi quwa 59 cinaancho quwa (3) nna (4) worroonnihu agarame heereenna wo'naalshu aana noo mootimmate loosaasinchi loosu korkaatinni dagganno xisso woy loosu aana heereenna iillitanno gawajjo korkaatinni loosunni gatinoha ikkiro gudinokkita wo'naalshu yanna xissotenni woy gawajjotenni woyyaawihu gedensaanni gudanno gede assinanni.

6. Wo'naalshu aana no mootimmate loosaasinchi wolqate aleenni ikkino korkaatinni mittu agani woroonni ikkitino yannara loosunni gatannoha ikkiro loosu aana leelli yanna calla keenne loosu jeefishshasi wonshinanniha ikkanno.

7. Konni quwi cinaanchu quwi 5 iima worroonnihu heerirono ilate korkaatinni mittu agani aleenni ikkitino yannara loosu aana leeltinokki wo'naalshu yanna loosaasincho ilate fajjose gooffu gedensaanni wo'naalshu yannase guddanno gede assinanni; loosu aana leeltinokki yanna mittu aganinni ajjannota ikkituro kayinni loosu jeefishshi keeno loosu aana keeshshitu

ከአንድ ወር በታች በሥራው ላይ ካልተገኘ በሥራው ላይ የተገኘበት ጊዜ ብቻ ታስቦ የሥራ አፈጻጸም ይሞላለታል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ የተደነገገው ቢኖርም በወሊድ ምክንያት ከአንድ ወር በላይ በሥራዋ ላይ ያልተገኘች የሙከራ ሠራተኛ የወሊድ ፈቃዷ እንደተጠናቀቀ የሙከራ ጊዜ እንድትጨርስ ይደረጋል፤ ሆኖም በሙከራ ሥራዋ ላይ ያልተገኘችበት ጊዜ ከአንድ ወር በታች ከሆነ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቷ በሥራ ላይ በቆየችበት ጊዜ ታስቦ ይሞላላታል፡፡

8. በሌላ ሕግ ካልተደነገገ በስተቀር በሙከራ ላይ ያለ የመንግሥት ሠራተኛ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ የመንግሥት ሠራተኛ ያለው መብትና ግዴታ ይኖረዋል፡፡

9. በሙከራ ላይ ያለን የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም ወቅቱን ጠብቆ ያልሞላ የሥራ ኃላፊ በዲሲፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡

20. ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ ስለመሆን

1. በሙከራ ጊዜው መካከለኛ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ያስመዘገበ የመንግሥት ሠራተኛ በቋሚነት መቀጠሩን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይሰጠዋል፡፡
2. በሙከራ ላይ የሚገኝ የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ጊዜውን ጠብቆ ያልተሞላለት እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 19(3) እና (4) የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ

yannata hedatenni wonshinanniha ikkanno.

8. Wolu seerinni worroonnihu agarame heereenna wo’naalshu aana noo mootimmate loosaasinchi wo’naalshu yannasi gudino loosaasinchi ledo taalo qoossonna gadacho heedhannosi.

9. Wo’naalshu aana noo mootimmate loosaasinchi loosu jeefishshi keeno yanna agare wonshinokki loosu sooreessi disipiliinetenni xa’mamannoha ikkanno.

20. Uurrinshu Mootimmate Loosaasinchimma

1. Wo’naalshshu yannara assinoonni keenora mereerimanna ale ikkinoha loosu jeefishshi guma abbinohu mootimmate loosaasinchi uurrinshunni qaxaramasi xawissanno borro uyinannisi.

2. Wo’naalshu yannara qaxaramino loosaasinchi loosu gumulshi guma yanna agare wonshinoonnikkiha ikkiro konni lallawi quwa 19(3) nna (4) worroonniri noo gedeenni heereenna mittu agani giddo loosisi gumulshi keeno assinanniha ikkanna wo’naalshaho qaxarami yannanni hananfe uurrinshunni mootimmate loosaasincho ikkanno.

21. Yannate Geeshshi Loosaasincho Qaxara

1. Konni quwi cinaancho quwa 2 woro agarante heedheenna aye mootimmate loosu mini yannate geeshshi loosaasincho qaxadhara dandaannohu hegeraamu akati nookki loosu

ሆነው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የሥራ አፈጻጸም ምዘና እንዲሞላ ተደርጎ ለሙከራ ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ ቋሚ የመንግሥት ሠራተኛ ይሆናል፡፡

21. ጊዜያዊ ሠራተኛ ስለመቅጠር

1. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጊዜያዊ ሠራተኛ ሊቀጥር የሚችለው የዘላቂነት ባሕርይ በሌለው ሥራ መደብ ላይ ነው፤ ሆኖም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ ጊዜያዊ ሠራተኛ መቅጠር ይችላል፡፡
2. አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከፍተኛ ባለሙያ ለሚጠይቅ ማናቸውም ክፍት የሥራ መደብ በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር ወይም በቅጥር ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ለማግኘት የማይቻል መሆኑን በማረጋገጥ የውጭ አገር ዜጋ በጊዜያዊነት ሊቀጥር ይችላል፡፡
3. ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜጋ ጊዜያዊ ሠራተኞች አቀጣጠር፣ የሚኖራቸው መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚጠበቁላቸው የሥራ ሁኔታዎች ዝርዝር ሁኔታ የመስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

22. ሥራዎችን በውል በሦስተኛ ወገኖች ስለማሠራት

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሮውን በማስፈቀድ የሕዝብን ጥቅም በማይጎዱ የተወሰኑ የሥራ መደቦችን ወይም

madaweraati; ikkirono, ikkito gadadissuro uurrinshu madawe aana yannate geeshshi loosaasincho qaxadhara dandaanno.

2. Mittu mootimmate loosu mini aliidi ogeessa xa'mitanno aye loosu madawera qixiretenni, soorrishshunninna deerru lophonni Itophiyu qansicha ikkino ogeessa afira hoogiro wole gobba qansicha yannate geeshshira qaxadhara dandaanno.

3. Itophiyu woy gobba qansicha yannate geeshshira qaxadhate, heedhannosi qoossonna gadacho hattono agarrasiha hasiissanno loosu ikkito tittiro Jeefisiisaanote Amaale Mini Wodhonni murranni.

22. Looso Sheemaatunni Sayikki Bissara Uyne Loosiisa

1. Hasiise leelliro aye mootimmate loosu mini biiro fajjishiishiratenni daga gawajjitannokki batidhinokki loosu madabba woy loossa hallanya uurrinshuwara woy wole uurrinshuwara sheemaatunni sayisatenni loossanno gede assara dandaanno.

2. Hallanya uurrinshuwaranna wole uurrinshuwara sayisa dandiinanni loossa lainohunni biiro tittirshunni jeefishshu biddissa fushshitanno.

23. Mootimmate Loosaasincho Guto Qaxadha

1. Mootimmate loosu minna mittu mootimmate loosaasinchi addi egennonna ogimmate

ሥራዎችን ለግል ድርጅቶች ወይም ለሌሎች ተቋማት በውል በማሸጋገር እንዲሠሩ ማድረግ ይችላል፡፡

2. ለግል ድርጅቶችና ለሌሎች ተቋማት በውል ሊሸጋገሩ ስለሚችሉ ሥራዎች ቢሮው ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

23. የመንግሥት ሠራተኞችን በጋራ ስለመቅጠር

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የተለየ እውቀት እና የሙያ ክህሎት ለሥራቸው በጣም አስፈላጊ መሆኑን ሲረዱ በጋራ ሊቀጥሩ ይችላሉ፡፡

2. የሚቀጥሩበትን ሁኔታ፣ ቅጥሩ የሚቆይበትን ጊዜ፣ የደመወዝ አከፋፈል እና የሥራ ሁኔታዎችን ቢሮ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡

ንኡስ ክፍል ሁለት

<u>የደረጃ ዕድገት</u>

24. የደረጃ ዕድገት ዓላማ

የደረጃ ዕድገት ዓላማ ሥራው ብቃት ባለው ሠራተኛ እንዲከናወን ለማስቻል፣ የመሥሪያ ቤቱን የሥራ ውጤት ለማሻሻል እና ሠራተኛውን ለማበረታታት ነው፡፡

25. የደረጃ ዕድገት አሰጣጥ

1. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ለደረጃ እድገት ለመወዳደር በአዋጁ አንቀጽ 12(1) መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

2. የሙከራ ጊዜውን ያላጠናቀቀ

dandoo loosinsara lowo geeshsha hasiissannota ikkase huwatturo guto qaxadhitara dandiitanno.

2. Qaxadhitanno ikkito, qixire keeshshitanno yanna, damoozu baatooshshenna wole loosu ikkituwa biiro fushshitanno biddissinni murranni.

Cinaancho Gafa Lame

Deerru Lopho

24. Deerru Lopho Hexxo

Deerru lopho hexxo loosu ikkadimma noosi loosaasinchinni loosamanno gede assate, loosu miniha loosu jeefishsha woyyeessate hattono loosaasincho jawaachishateeti.

25. Deerru Lopho Uynanni Gara

1. Ayehuno mootimmate loosaasinchi deerru lophora heewisamate konni lallawi quwa 12 cinaancho quwa 1 garinni dandoote ikkadimma buuxishshi taje shiqisha noosi.
2. Wo'naalshu yannasi gudinokkihu mootimmate loosaasinchi deerru lophora heewisama didandaanno.
3. Deerru lopho uynanni wolootta amanyootubba lainohunni biiro biddissa fushshitara dandiitanno.

Cinaancho Gafa Sase

Soorrishshanna Diliddile

26. Giddo Soorrishsha

የመንግሥት ሠራተኛ ለደረጃ ዕድገት መወዳደር አይችልም፡፡

3. የደረጃ ዕድገት ስለሚሰጥበት ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

ንኡስ ክፍል ሦስት

ዝውውርና ድልድል

26. የውስጥ ዝውውር

1. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ግልጽ የሆነ አሠራርን በመከተል የመንግሥት ሠራተኛን በዚያው መሥሪያ ቤት ውስጥ እኩል በሆነ የሥራ ደረጃና ደመወዝ ወደ ሌላ የሥራ መደብ ወይም ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ ሥራ ቦታ በማዛወር ሊያሠራ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በመሥሪያ ቤቱ ላይ አደጋ እንዳይደርስ ለመከላከል ወይም አደጋው ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ሲባል ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዙ ሳይቀነስ፣ ደረጃው ወይም የሥራው ዓይነት ሳይጠበቅ አንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ በጊዜያዊነት አዛውሮ ማሠራት ይችላል፡፡
3. የመንግሥት ሠራተኛ በጤና መታወክ ምክንያት በያዘው የሥራ መደብ ወይም ባለበት የሥራ ቦታ ላይ ሊሠራ አለመቻሉ በሐኪም ማስረጃ ሲረጋገጥ፡-

   ሀ) በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ መደብ ካለ በያዘው

1. Mootimmate loosu mini loosoho hasiise leelliro xawo ikkitino ha’rinsho harunsatenni mootimmate loosaasincho hakkonni loosi mine taalo ikkino loosu deerrinninna damoozinni wole loosu madawera woy mitte loosu basenni wole loosu basera soorrishshunni loosiisara dandaanno.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 aana worroonnihu hee’reenna loosu minira dano iillitannokki gede gargarate woy dano iillishshino gawajjo taashshate aye mootimmate loosaasinchi damoozasi xeinsikkinni, deerra woy loosu dana agara hasiissukkinni mitto diro sa’inokki yannara yannate geeshsha soorrishshunni loosiisara dandaanno.
3. Loosaasinchu fayyimmate mitiimma korkaatinni amadino loosu madawera woy loosu basera loosa dandaannokkita hakimete booride tajenni buunxiro:
   a) Taalu deerrinni gaamamara dandaanno fano loosu madawe heedhuro amaddino deerrinni, woy
   b) Taalu deerrinni gaamamara dandaanno fano madawe hoogguronna Loosaasinchu woffi yitino madawe aana loosate fajjaameessa ikkiro deerrasi woffi assine sumuu yitannosi loosu madawe woy loosu base soorrine loosiisa dandiinanni.
4. Aye mootimmate loosaasinchi madawe faaqantinoha ikkiro taalo deerra afidhino wole madawera soorrine loosiisa

ደረጃ፣ ወይም

ለ)በተመሳሳይ ደረጃ ሊመደብ የሚችልበት ክፍት የሥራ መደብ ከሌለና ሠራተኛው ዝቅ ባለ ደረጃ ላይ ለመሥራት ፈቃደኛ ከሆነ ደረጃው ተቀንሶ ወደ ሚስማማው የሥራ መደብ ወይም የሥራ ቦታ ይዛወራል፡፡

4. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ ተመሳሳይ ደረጃ ወዳለው የሥራ መደብ ማዛወር ይቻላል፡፡
5. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ሠራተኛውን ለመመደብ በመስሪያ ቤቱ ተመሳሳይ ስራ መደብና ደረጃ ያልተገኘ እንደሆነ ቢሮው በሌሎች የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በሚገኙ ክፍት የስራ መደቦች ይመድባል፡፡

27. በተጠባባቂነት ማሠራት

1. ሁኔታዎች ሲያስገድዱ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከፍ ያለ ደረጃ ባለው የሥራ መደብ ላይ በተጠባባቂነት እንዲሠራ ማድረግ ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ከአንድ ዓመት በላይ ለሚፈጅ ትምህርት ወይም ስልጠና የሄደን የመንግሥት ሠራተኛ ለመተካት ትምህርቱ ወይም ሥልጠናው ለሚፈጀው ጊዜ ድረስ የሥራ መደቡን ግልጽ በሆነ መስፈርት በውድድር በተጠባባቂ ሠራተኛ ማሠራት ይቻላል፡፡
3. ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ

dandiinanni.

5. Konne quwa cinaancho quwa 4 aana xawinsoonni garinni loosu mini giddo taalo deerra afidhino loosu madawe hoogguro biiro wole loosu minnara gaantanno.

27. Agadhaanchimmatenni Loosiisa

1. Ikkito gadadissuro aye mootimmate loosaasincho mitto diro sa'inokki yannara luphi yino deerra afidhino loosu madawera agadhaanchimmatenni gaamme loosanno gede assa dandiinanni.
2. Konne quwa cinaancho quwa 1 woro heedhurono mittu diri aleenni keeshshanno roso woy qajeelsha harino mootimmate loosaasincho riqiwate rosu woy qajeelshu keeshshanno yannara loosu madawe xawo ikkino bikkaasinchinni heewinse agadhaanchu loosaasinchinni loosiisa dandiinanni.
3. Mootimmate loosaasincho agadhaanchimmatenni loosanno gede assinanni yannara agadhaanchimmate baatooshshe baantanni. Tittirsha biddissunni murranni.

28. Wolu Loosu Mininni Assinanni Soorrishsha

1. Mootimmate loosu mini loosoho hasiisiha ikkiro xawo ikkino egensiishsha fushshatenni heewisiise adhannonna soyaanno loosu mini hattono loosaasinchu sumuummenni taalu deerrinna damoozinni biirote afamooshshinni

በተጠባባቂነት እንዲሠራ ሲደረግ የተጠባባቂነት አበል ይከፈለዋል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

28. ከሌላ መሥሪያ ቤት የሚደረግ ዝውውር

1. ማንኛውም የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ግልጽ ማስታወቂያ በማውጣትና በማወዳደር ላኪና ተቀባይ መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ሠራተኛው ሲስማሙ ማንኛውንም የመንግሥት ሠራተኛ እኩል በሆነ ደረጃና ደመወዝ ቢሮውን በማሳወቅ አዛውሮ ማሠራት ይችላል፡፡
2. የሚመለከተው የመንግሥት ሠራተኛ በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤት እና በየደረጃው የሚገኝ መንግሥት መሥሪያ ቤት ሲስማሙ በክልሉ ዝውውርን ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሲያጸድቀው ማንኛውንም የመንግሥት ሠራተኛ እኩል በሆነ ደረጃና ደመወዝ አዛውሮ ማሠራት ይቻላል፡፡
3. በተመሳሳይ ደረጃ ለመቀጠር አመልክቶ በውድድሩ የተመረጠ የመንግስት ሠራተኛ በዝውውር ሥርዓት እንዲመደብ ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚዛወር ሠራተኛ የክልሉ መንግሥት ሠራተኞች ሕግ በሚያዘው መሠረት በያዘው የሥራ ደረጃና በአገልግሎት ዘመኑ ምክንያት ያገኝ የነበረው ደመወዝና መብቶቹ አይቀነሱበትም፡፡
5. የትዳር አጋሮችን ለማገናኘት ሲባል አንድን

soorrishshunni adhe loosiisa dandaanno.

2. Mootimmate loosu minna noonsa sumuummenni loosaasine soorrishshunni adhitannonna sokkanohu biiro soorrishsha kaajjishshuro calla ikkanno.

3. Taalu deerrira qaxaramate shiqe heewotenni dooraminohu mootimmate loosaasinchi soorrishshu amanyootinni gaamamanno gede assinanni.

4. Konne quwa cinaancho quwa 5 worroonnihu agarame heereenna, konni quwi garinni soorrishsha assinanni loosaasinchi qoqqowu mootimma loosaasine seeri woranno garinni amaddino loosu deerrinninna owaatesi yanna kaiminni afiranno damoozanna qoosso dixeinsanni.

5. Galtenna galtaama mitteenni heerate qoosso ayirrisate taalu deerrinna damoozinni, taalu deerrinna damoozi hoogiro loosaasinchu sumuummenni woffi yino deerrira soorrishsha assine loosiisa dandiinanni.

29. Argete Soorrishsha

1. Hasiise leelleenna aanno loosu mininna loosaasinchu sumuu yituro mootimmate loosaasincho wole mootimmate loosu mine, mootimmate latishshu uurrinshara woy mootimmaweello uurrinshara mitto diro sa'inokki yannara argete soorrishsha assine loosanno gede assa dandiinanni.

2. Mootimmate loosu mini hasiisiha ikkiro

የመንግስት ሠራተኛ በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ፣ ተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ ካልተገኘ በሠራተኛው ስምምነት ዝቅ ባለ ደረጃ አዛውሮ ማሰራት ይቻላል፡፡

29. የትውስት ዝውውር

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ላኪው የመንግሥት መሥሪያ ቤትና ሠራተኛው ሲስማሙ አንድን የመንግሥት ሠራተኛ በሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ወይም በመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ወዳልሆኑ ድርጅቶች ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በትውስት ተዛውሮ እንዲሠራ ማድረግ ይቻላል፡፡
2. ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከመንግሥት ልማት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት ማንኛውንም ሠራተኛ ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በትውስት አዛውሮ ማሠራት ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የክልሉ መንግሥት በሕዝብ ላይ የሚደርስ ድንገተኛ አደጋን ለመከላከል ወይም አደጋው ያደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል ሲባል ማንኛውንም የመንግሥት ሠራተኛ በያዘው ደመወዝ በክልሉ ከአንድ አስተዳደር እርከን ወደ ሌላ አስተዳደር እርከን ወደሚገኝ መንግሥት መሥሪያ ቤት ለአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በትውስት አዛውሮ ማሠራት ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በትውስት የተዛወረ ሠራተኛ፡-

mootimmate latishshu uurrinsha woy mootimmaweello uurrinsha loosaasincho mitto diro as’inokki yannara argete soorrishshinni loosanno gede assa dandaanno.

3. Konne quwa cinaancho quwa 1 worroonnihu heerirono qoqqowu mootimma dagate aana iillitanno hedeweelcho dano gargarate woy dano iillishshino gawajjo taashshate aye mootimmate loosaasincho amadino damoozinni qoqqowoho mittu gashshootu taqinni wole gashshootu taqira afamanno mootimmate loosu mine mitto diro sa’inokki yannara argete soorrishshinni loosiissara dandiitanno.

4. Konne quwa cinaancho quwa 1 garinni soorrishsha assinoonni loosaasinchi:

   a) Damoozunna wole horo xe’ukkinni argete soorrishshinni adhe loosiisiranno loosu mininni jeefinsanniha ikkanno.

   b) Loosu jeefishsha argete soorrishshinni adhe loosiisannosi loosu mini widoonni wonshine ama loosu minira sayinsanni.

   c) Disippiliinete huno loosiro argetenni adhe loosiisanno loosu mini tittirshu tajenna naqqaso ledo ama loosu minira egensiisannoha ikkanna ama loosu minino hajo buuxatenni hasiissanno qaafo adhanno.

ሀ)ደመወዝና ማንኛውም ጥቅሙ በዝውውሩ ምክንያት ሳይጓደል በትውሰት አዛውሮ በሚያሰራው መስሪያ ቤት ይፈጸምለታል፤

ለ)የሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤቱ በትውሰት አዛውሮ በሚያሰራው መስሪያ ቤት ተሞልቶ ለቀጣሪው መሥሪያ ቤት ይተላለፋል፤

ሐ) የዲሲፕሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ በትውስት ተቀባዩ መስሪያ ቤት ለቀጣሪ መሥሪያ ቤቱ ከዝርዝር ማስረጃ ጋር ያሳውቃል፣ ቀጣሪ መሥሪያ ቤቱም ጉዳዩን አጣርቶ እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

30. ድልድል

1. የመንግሥት መሥሪያ ቤት አዲስ አደረጃጀት አጥንቶ ተግባራዊ ሲያደርግ ሠራተኞቹን በማወዳደር ደልድሎ ማሠራት አለበት፡፡
2. በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚገኝ ክፍት የሥራ መደብ ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚደለደል የመንግሥት ሠራተኛ እንዲያዝ የሚደረገው መሥሪያ ቤቱ የተዘጋ ወይም ትርፍ የሰው ኃይል ሲኖረው ወይም የሥራ መደቡ የተሰረዘ ከሆነና ድልድሉን ቢሮው ሲወስን ወይም ቢሮው በክልሉ መንግስት ሲታዘዝ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚደለደል ሠራተኛ ቀደም ሲል ይዞት በነበረው ደረጃና በአገልግሎት ዘመኑ ምክንያት ያገኝ

30. Diliddile

1. Mootimmate loosu mini haaro tantano xiinxalle loosu aana hosiisanno yannara loosaasinesi heewisiisatenni daladdale loosiisanno.

2. Aye mootimmate loosu mini giddo afantanno fano loosu madawe wolu mootimmate loosu mininni abbine daladdallanni mmotimmate loosaasinchinni amadantanno gede assinannihu loosu mini cufaminoha woy tirfe mannu wolqa heedhuro woy albaanni nooti loosu madawe faaqantinoha ikkironna dildile assinanni gede biiro gumultinoha ikkiro woy biiro qoqqowu mootimma hajajjuha ikkiro callaati.

3. Konni quwi garinni dilidile assinanni loosaasinchi albaanni amadino deerrinni owaantete yannasi kaiminni afiranno damoozinna wole horo dixeinsanni.

Cinaancho Gafa Shoole

<u>Loosu Jeefishsha</u>

31. Loosu Jeefishshi Keeno

1. Loosu jeefishshi keeno hexxo loosu mixo kaima assitinota ikkite:

   a) Aye mootimmate loosaasinchi loososi agarranni geeshshinni, islanchimmanni, yannanna fulo xeisino garinni loosanno gede assate;

   b) Sufamino garinni loosu jeefishshi

የነበረው ደመወዝና ጥቅሞቹ አይቀነሱበትም፡፡

ንኡስ ክፍል አራት

<u>የሥራ አፈጻጸም</u>

31. **የሥራ አፈጻጸም ምዘና**

1. የሥራ አፈጻጸም ምዘና ዓላማ በሥራ እቅድ ላይ የተመሠረተ ሆኖ፡-

   ሀ) ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሥራውን በሚጠበቀው መጠን፣ ጥራት፣ ጊዜ እና ወጪ በተሟላ ሁኔታ እንዲያከናውን ለማድረግ፣

   ለ) ተከታታይ የሥራ አፈጻጸም ምዘና በማካሄድ የመንግስት ሠራተኛውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ቀጣዩ የሥራ አፈጻጸሙ እንዲሻሻል በማድረግ ውጤታማ እንዲሆን ለማብቃት፣

   ሐ)የመንግሥት ሠራተኛውን የሥልጠናና የመሻሻል ፍላጎት በትክክል ለይቶ ለማወቅ፣

   መ) በውጤት ላይ የተመሠረተ ማትጊያ ለመስጠት፣

   ሠ) የመንግስት መሥሪያ ቤቱ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመሥርቶ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን እንዲሰጥ ለማስቻል ነው፡፡

2. በመንግስት መስሪያ ቤት የሚከናወን የሥራ አፈጻጸም ምዘና ሥርዓት፣

keeno assatenni mootimmate loosaasinchita kaajjadonna laafa midaado bande aantetenni loosu jeefishshisi woyyaawanno assatenni gumaamonna ikkado ikkanno assate;

c) Mootimmate loosaasinchita qajeelshunna woyyaambete hasatto bade afate;

d) Guma kaima assino afansha aate;

e) Mootimmate loosu mini buuxantino taje kaima assire gashshootu gumulo aanno gede dandiisiisate;

2. Mootimmate loosu mini giddo assinannihu loosu jeefishshi amanyooti:

   a) Xawonna buuxantino taje aana kaima assinoha ikke gumu keeno assate dandiisiisannoha;
   b) Loosamino loosi gaammoonni baajeette, yanna, geeshshinna islanchimma ledo heewinseenna halaalanya guma keenate dandiisiisannoha;
   c) Gaamotenni loosanna gutu kakkaooshshe halashshannoha;
   d) Mootimmate loosaasine woy gaamote mereero keeraancho heewo kalaqatenni uurrinshate guma woyyeessate kaa'lannoha;
   e) Jeefishshu sufaminonna mimmitu ledo xaadooshshu noonsa loossa mereero mittu wolu gumi aana gashshanno hekko keenate dandiisiisannoha;

ሀ) ግልጽና በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሠረተ የውጤት ምዘና ለማከናወን የሚያስችል፣

ለ)የተከናወነው ሥራ ከተመደበው በጀት፣ ጊዜ፣ መጠንና ጥራት ጋር በማነጻጸር ትክክለኛውን ውጤት ለመመዘን የሚያስችል፣

ሐ)የቡድን አሠራርንና የጋራ ተነሳሽነትን የሚያጎልበት፣

መ) በመንግሥት ሠራተኞች ወይም ቡድኖች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስን በመፍጠር ተቋማዊ ውጤትን ለማሻሻል የሚያግዝ፣

ሠ)በአፈጻጸም ተከታታይነትና ተመጋጋቢነት ባላቸው ሥራዎች መካከል አንዱ በሌላኛው ውጤት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ ለመገምገም የሚያስችል፣ መሆን አለበት፡፡

3. የስራ አፈጻጸም ምዘና ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸማል፡፡

32. የደመወዝ ጭማሪና ማበረታቻ አወሳሰን

1. የመንግሥት ሠራተኛ የደመወዝ እርከን ጭማሪ የሚያገኘው በሥራ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ላይ በመመስረት በየሁለት ዓመቱ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አፈጻጸም ውጤትን መሰረት በማድረግ ለመንግስት ሠራተኛ ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

ikka noosi.

3. Loosu jeefishshi keeno biiro fushshitanno biddissi garinni jeefinsanni.

32. Damoozu Lexxonna Afanshshu Jeefishsha

1. Mootimmate loosaasinchi damoozu giddaasinchi lexxo afirannohu loosisi jeefishshi keeno kaiminni lamu lamu diri gawalora ikkanno.
2. Konni quwi cinaancho quwa 1 woro agarante heedheenna loosu jeefishshi guma kaima assatenni mootimmate loosaasinchira afansha uyinanni.
3. Biiro loosu jeefishsha keennanni amanyoote, giddaasinchu lexxo hattono jawaachishate uyinanni afanshi ikkito tittirshunni jeefishshu biddissa fushshitanno.

GAFA SHOOLE

<u>LOOSU YANNANNA FAJJO</u>

Cinaancho Gala Mite

<u>Loosu Yanna</u>

33. Rosantino Loosu Yanna

Mootimmate loosaasineti rosantino loosu yanna loosu akati garinni gumullannita ikkite mitte lamalara 39 sa’’aate sa’inota ikka dinose.

34. Loosoho E’nanninna Fullanni Sa’’aate

Mootimmate loosaasine loosoho e’annonna

3. ቢሮው የሥራ አፈጻጸም ምዘና ስለሚከናወንበት ሥርዓት፣ የእርከን ጭማሪ እና ማበረታቻ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡፡

ክፍል አራት

<u>የሥራ ሰዓትና ፍቃድ</u>

ንኡስ ክፍል አንድ

<u>የሥራ ሰዓት</u>

33. መደበኛ የሥራ ሰዓት

የመንግሥት ሠራተኞች መደበኛ የሥራ ሰዓት እንደየሥራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በሳምንት ከ 39 ሰዓት መብለጥ የለበትም፡፡

34. የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት

